ሲን አንድ

እቤት ውስጥ ምሳ ሰአት

የበአል ቀን ነው። መሃከለኛ ኑሮ ያላቸው በተሰቦች ቤት። እቤት ውስጥ ተንዘጉዞ የሃበሻ በአል ድባብ ይታያል። እንደአስፈላጊነቱ ዳቦ ቡና ምናምን ያታያል። አባት ባህላዊ ልብስ ለብሰ ለብሶ ሶፋው ላይ ተቀምጦ ይታያል። እናት ደፋ ቀና ትላለች። ምግብ እያቀራረበች።

አባት

ማምጫቸው እኮ ደረሰ። አሰነዳድተሽ አልጨረሽም?

እናት

አሁንማ ጨራረስኩ።

(ከውጪ የገበ ሀ ሻ ልብስ የለበሰች ሴት ልጅ አስከትላ ትገባለች። ልጃቸው ናት። የፀሃይ መነፅር አድርጋለች። እየተቃቀፉ ሰላም ይባባላሉ።)

አባት

(በር በሩን እያዩ)

ልጅ

(እናቷን እየሳመች በመሳቀቅ ወደ አባቷ ዞራ)

አባዬ አልተመቸውም ሆኖበት ነው። ይቅርታ ብሎሃል።

አባት

ንቀት ነው እንጂ። በበአል ምን የማያስመች ነገር ገጥሞት ነው? ቤተሰባዊነቱን አልፈልገውም ማለቱ እንጂ

እናት

አረፍ በይማ እስኪ ትረፍበት

(ህፃኑን እየሳሙ)

አባት

(ነገር እየበሉ መሆኑ በሚያሳብቅ ሁኔታ ተቀምጠው ይታያሉ)

ህምምም

(ምግብ ቀርቦ ሊበላ ሲል)

መነፅርሽን ከአይንሽ ላይ አንሽው እንጂ ልጄ ነውርም አይደል እንዴ?

(እየተሳቀቀች መነፅሯን ስታወልቀው አይኗ በልዞ ያታያል። ታቀረቅራለች)

አባት

አበስኩገበርኩ!!! ምንድነው የማየው? ይሄ ምናምንቴ ዛሬም ደብድቦሽ እንዳይሆን?

ልጅ

(ወደ ልጇ እያሳየቻቸው)

አባዬ? እረፍ ምንም አይደለም።

እናት

ኪዳነምህረት ምን አልኩሽ?

አባት

(ወደ ህፃኑ ዞረው ንዴታቸው ሳይበርድ ጥርሳቸውን እንደነከሱ)

ጎሽ ሚኩ እስቲ ወደውጪ ብቅ በልና ልጆች አሉልህ ተጫወት

እናት

እህሉ ተበልቶ አይሻልም የመቅደስ አባት?

(ህፃኑ ተፈትልኮ ይወጣል,)

አባት

ከልጇ መጠቃት እህሉ ይቀድማል ስናፍቅሽ? ይህ የማይረባ ስራውን ስለሚያውቅ ነዋ ያልመጣው።

(በመቆጨት በእግራቸው መሬቱን እየደቁ)

ልጅ

አባዬ አታክብደው ብዙም አይደለም እኮ

አባት

(ተጠግተው አገላብጠው እያዩአት)

ምኑን አስተረፈሽ? ምን እስኪሆን ነው የምትጠብቂው? አልበዛም? እኔ አባትሽ እያለሁ?ጥንቅር ብሎ ለምን አይቀርም

አስፈላጊ ከሆነ ህግ ፊት እገትረዋለሁ። የኔ ልጅ አይደለሽ እንዴ? አንድ ልጄን የማንም እጅ እንዲያርፍብሽ አድርጌ አላሳደግኩሽም።

ልጅ

እኮ!! ያንተ ልጅ ስለሆንኩ እኮ ነው ዱላን ችዬ መኖር ያወቅኩበት

አባት

እንዴት እንዴት?

ልጅ

(እየተረከች በመሃል ምስሎች ይታያሉ።)

{አየህ ልጅ ሆኝ እማዬን ስትሰድባት ባል የሚደበድብ እንደሆነ ለአንድ ልጅህ እያስተማርከኝ እንደነበር አላስተዋልክም። ልጅህን ምንም ሳይጎልብኝ አቅብጠህ ስታሳድገኝ እንደ ሚንሰፈሰፍልኝ አባቴ ብቻ የምስልህ እንጂ እንደከፋ ባል እንደተሳልክብኝ አላስተዋልክም።}

ሲን ሁለት

እዛው ቤት ፍላሽ ባክ

እናትየውን አባትየው በጥፊ ሲመታት ልጅቷ በር ስር ተለጥፋ ስታያቸው ይታያል። አባትየው እየጮኸ ያታያል, ድምፁ አይሰማም በትረካው ይሸፈናል።

አባቴ ነህ። የምትሳሳልኝ ልጅህ። ካንተ የተቀዳሁ ፀበል። ባንተ ኩትኳቶ ያደግኩ ያንተ ፍሬ ወንድ አባት ሲሆን የሚራራ ባል ሲሆን የሚጨክን እንደሆነም ያስተማርከኝ አንተ ነህ አባ። አንተም በልጅህ ሲሆን አንገበገበህ ጥቃት ሆኑብህ በሚስትህ ሲሆን ግን «የተለመደ የባልና የሚስት ፀብ ነው» ነበር የምትለው።

ጥንቅር ብሎ ለምን አይቀርም

(አባት አንገታቸውን ደፍተው ይታያል። እናት በመሃረባቸው እንባቸውን ይጠርጋሉ።_)